## የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
## የፍትሀ ብሔር ክፍል

☐ Civil Actions Branch (የፍትሐ ብሔር እርምጃዎች ቅርንጫፍ)
500 Indiana Ave., N.W.
Room 5000
Washington, D.C. 20001
ስልክ: (202) 879-1133

☐ Landlord & Tenant Branch (የአከራይ እና ተከራይ ቅርንጫፍ)
510 4th Street, N.W.
Room 110
Washington, D.C. 20001
ስልክ: (202) 879-4879

☐ Small Claims & Conciliation Branch (አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች እና የማስታረቅ ቅርንጫፍ)
510 4th Street, N.W.
Room 120
Washington, D.C. 20001
ስልክ: (202) 879-1120

______________________________________፣ ከሳሽ

v. መዝገብ ቁጥር:- ______________________________

______________________________________፣ ተከሳሽ

### የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የወጣ ተጨማሪ ማዘዣ
### ( የባለዕዳ ግለሰብ የደሞዝ፣ ገቢ፣ ምንዳ፣ ጥቅማጥቅሞች፣ እና የጡረታ ገንዘብ ፍርድ ቤቱ ለፈረደለት ግለሰብ እንዲሰጥ የመጠየቂያ ትዕዛዝ)

ለ:____________________________________________________________

ፍርድ ቤቱ ድርጅታችሁ በዚህ ክስ መዝገብ ላይ ተከሳሽ የሆነውን፣ ______________________________፣ ቀጣሪ ድርጅት እንደሆናቹህ መረጃ ደርሶታል። ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር በነበረው ክስ መዝገብ ላይ የካሣ ክፍያ ተፈርዶለቸዋል። የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የወጣው ተጨማሪ ማዘዣ የእናንተ ድርጅት (1) በተከሳሽ የቅጥር ሁኔታ ላይ ለሚቀርቡት ለሁሉም ጥያቄዎች የተሟላ መረጃ እንድትሰጡ፣ እና (2) በፍርድ ቤቱ የተበየነው የገንዘብ መጠን ሙሉ ለሙሉ እስከሚከፈል ድረስ፣ ወይም ፍርድ ቤቱ ሌላ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ማንኛውም የተከሳሽን ገቢ ገንዘብ በመቁረጥ ለከሳሽ እንድትከፍሉ ብያኔ አስተላልፏል።

እባካቹህ መመሪያዎቹን በጥሞና አንብቡ እና ከታች ለተቀመጡት ጥያቄዎች በጥንቃቄ መልሱ ስጡ። ይሄንን የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባገኙ አስር (10) የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ የማትሰጡ ከሆነ፣ ተከሳሽ የሚገባቸውን ሁሉንም የካሣ ገንዘብ መጠን፣ ወለድ እና ሌሎችን ወጪዎችን ጨምሮ፣ እንደ አሰሪ ድርጅት እንፍትከፍሉ ፍርድ ቤቱ በድርጅታቹህ ላይ ትዕዛዝ ያወጣል።

**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የፍትሀ ብሔር ክፍል**

ጠበቃ ለተከሳሽ

አድራሻ

ስልክ

ኢ-ሜይል አድራሻ

የጸደቀው በ፡- ምክትል የፍርድ

የጸደቀበት

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
የፍትሀ ብሔር ክፍል

**<u>በአሰሪ ድርጅቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች-የአደራ ስምምነት ፈፃሚው</u>**

ይሄ የፍርድ ቤት ማዘዣ በወጣ አስር (10) ቀናት ጊዜ ውስጥ፣ (1) በሀሰት መመስከር ሕገ ደንብን በማክበር ለሁሉም ከታች ለተቀመጡት ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለባቹህ፣ (2) የምትሰጡትን መልስ ለዚህ ፍርድ ቤት ማቅረብ አለባቹህ፣ እና (3) ቅጂውን ለከሳሽ እና ለተከሳሽ መስጠት ይኖርባቹሃል።

**(1)** ተከሳሽን ድርጅታቹህ የቀጠረ ከሆነ፣ ተከሳሽ የሚያገኙትን የተጣራ ደሞዝ መጠን (መመሪያ 3 ላይ እንደተጠቀሰው) ይጥቀሱ።

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

**(2)** ተከሳሽን ድርጅታቹህ የቀጠረ ከሆነ፣ እና ከዚህ ቀደም ለድርጅታቹህ በተፃፈ የፍርድ ቤት ማዘዣ ትዕዛዝ ለማክበር ከተከሳሽ ገቢ ወይም ደሞዝ ላይ በአሁኑ ሰዓት ገንዘብ እየቀረጣቹህ ከሆነ፣ ተቆራጭ ገንዘቡ የሚቀረጥላቸውን ግለሰብ ወይም ድርጅት ስም ይጥቀሱ፣ እና የፍርድ ቤቱን ስም እና የክስ መዝገብ ቁጥር ጨምሮ፣ የተቆራጩ ማዘዣ የወጣበት ሁሉንም ተገቢ መረጃ ይጥቀሱ፣

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

**(3)** በአሁኑ ሰዓት ተከሳሽ የድርጅታቹህ ተቀጣሪ ሰራተኛ ካልሆነ፣ ይሄ ፍርድ ቤት ማዘዣ ለእናንተ ድርጅት ከፃፈበት ቀን አንስቶ ላለፉት አራት ወራት ጊዜው ውስጥ ተከሳሽ የድርጅታቹህ ተቀጣሪ ነበሩ?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

**(4)** የተከሳሽ የስራ ቅጥር ውል የተቋረጠበት ቀን ________________________________________________።

---

ከላይ የሰጠሁት መልስ፣ እኔ እስከማውቀው እና እስከማገምነው ድረስ፣ በሀሰት መመስከር ሕግ መሰረት፣ እያንዳንዱ ፍሬ ሐሳብ ላይ እውነተኛ እና ትክለለኛ እንደሆኑ ምስክርነቴን እሰጣለሁኝ።

የተሟላው በቀጣሪ ድርጅቱ-የአደራ ስምምነት ፈፃሚው፡- ________________________________________
*ፊርማ፡-*

**ቀን፡-**______________________________ **ማዕረግ፡-** ________________________________________

**ስልክ**:______________________________ **ኢሜይል፡-** ________________________________________

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
የፍትሀ ብሔር ክፍል

## ለአሰሪ ድርጅቱ-አደራ ስምምነት ፈፃሚው መመሪያዎች

### 1. የስሌት ቀመር፡-

ተቆራጩ ገንዘብ የሚጠየቀው አንድ ተቀጣሪ ሰራተኛ በዲ.ሲ ውስጥ ከሚፈቀደው ዝቅተኛው የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን ሲባዛ በሳምንት ከ 40 ሰዓት በላይ ሰርቶ ገንዘብ የሚያገኝ ከሆነ ነው- በሌላ አገላለጽ፣ በዝቅተኛ የሚፈቀደው የሰዓት ደሞዝ ክፍያ መጠን ከ 40 ሙሉ ሰዓት ጊዜ ክፍያ በላይ አንድ ተቀጣሪ ሰራተኛ የሚሰራ ከሆነ ነው። የአደራ ስምምነት ፈፃሚው አሰሪ ድርጅት ተቆራጭ ገንዘብ ሲቆርጥ ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ የተቀመጠው በግዛቱ የሚፈቀደውን ዝቅተኛ የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን በሳምንት በ 40 ሲባዛ ጊዜ ለተቀጣሪ ሰራተኛው የሚደርሰው የተጣራ ክፍያ ገንዘብ የሚበልጥ ከሆነ አሰሪ ድርጅቱ 25% የሚሆን ተቆራጭ ያደርጋል። ክፍያ የሚፈጽመበት የጊዜ ሰሌዳ በየሳምንቱ ካልሆነ፣ አሰሪ ድርጅቱ ዝቅተኛው የሚፈቀደውን የደሞዝ የሰዓት ክፍያ መጠን በ 40 ያባዛና በመቀጠል የተገኘውን የብዜት ውጤት በክፍያ ጊዜው ላይ የተካተቱን የሙሉ እና/ወይም የከፊል ሳምንታቶችን ቁጥር ጋር ያባዛል። ይሄ ሲደረግ ተከሳሽ የገንዘብ ችግር የሚያጋጥመው ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተቀናሽ ገንዘቡን ሊቀንስ ይችላል።

### 2. የጊዜ ሁኔታ እና ቆይታ

በፍርድ ቤቱ የታዘዘው የክፍያ መጠን ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ፣ ወይም በፍርድ ቤት ሌላ ማዘዣ እስካልወጣ ድረስ፣ አሰሪ ድርጅቱ የተጠቀሰውን የክፍያ መጠን ከተቀጣሪ ሰራተኛው ላይ መቁረጥ እና የተቆረጠውን ገንዘብ እያንዳንዱ ወር ላይ ለሰራተኛው ደሞዝ ከተከፈለበት ወር ማብቃያ ቀን ጀምሮ በ 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን መክፈል አለበት።

### 3. ትንታኔዎች።

"ደሞዝ" ማለት ለግል የተሰጠ አገልግሎት የሚከፈል ወይም የሚከፈል ማካካሻ፣ እንደ ምንዳ፣ ደሞዝ፣ ኮሚሽን፣ ቦነስ፣ ወይም በሌላ መልኩ የሚከፈል ሲሆን በጡረታ ወይም በጡረታ መርሃ ግብር መሠረት የሚከፈሉ ወቅታዊ ክፍያዎችን ይጨምራል፡
"የተጣራ የደሞዝ ክፍያ" ማለት በሕግ ከታዘዙት ማንኛውም ተቆራጭ ገንዘብ ክፍያዎች ከተቀናነሱ በኋላ ለግለሰቡ የሚከፈለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን ነው። (D.C. Code § 16-571)

### 4. ተቆራጭ የሚደረገው ገንዘብ ስሌት።

ትክክለኛውን ተቆራጭ የሚደረገውን ገንዘብ ለማስላት፡-

(1) ለክፍያ ክፍለ ጊዜው የሰራተኛውን የተጣራ የደሞዝ ክፍያ መጠን ይወቁ።

(2) በዲ.ሲ ተግባራዊ የተደረገውን የሚፈቀደውን ዝቅተኛ የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠንን ደሞዝ የሚከፈልበት ቀን ላይ

በ 40 ያባዙ።

- ክፍያ የሚፈጽመበት የጊዜ ሰሌዳ የተለየ ከሆነ እና በየሳምንቱ ካልሆነ፣ ዝቅተኛው የሚፈቀደውን የደሞዝ የሰዓት ክፍያ መጠን በ 40 ማባዛት በመቀጠል የተገኘውን የብዜት ውጤት በክፍያ ጊዜው ላይ የተካተቱን የሙሉ እና/ወይም የከፊል ሳምንታቶችን ቁጥር ጋር ያባዙ።

(3) (1) ላይ የተገኘው መጠን ከ (2) ጋር የተገኘው መጠን ጋር እኩል የሚሆን ከሆነ፣ አሰሪው ድርጅት-የአደራ ስምምነት ፈፃሚው ምንም ዓይነት ተቀራጭ ከደሞዝ ላይ አይቀንስም።

(4) (1) ላይ የተገኘው መጠን ከ (2) ላይ ከተገኘው መጠን የሚበልጥ ከሆነ፣ በሁለቱ መጠኖች ላይ ያለውን ቅንስናሽ መጠን ተሰልቶ በ .25 መባዛት አለበት።

ማስታወሻ:- ከጁላይ 1 ቀን፣ 2019 ዓ.ም ጀምሮ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚፈቀደው ዝቅተኛው የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን $14.00 ነው። ዝቅተኛ የሚፈቀደው የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን ላይ ለወደፊቱ ሊመጡ የሚችሉ ማንኛውም ዓይነት ለውጦችን ቀጣሪ ድርጅቱ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። በ ዲ.ሲ. ሕገ ደንብ ቁጥር § 32-1003 (f-1) መሰረት፣ ማንኛውም በዝቅተኛ የሚፈቀደው የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን ላይ የሚደረግ ለውጥ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ጭማሬው በመርሀግብር ከመያዙ በፊት በ 30 ቀናት ጊዜ በፊት በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሬጅስትራር እና በስራ ቅጥር አገልግሎት መመሪያ [Department of Employment Services] ድረገጽ ላይ መጠቀስ እንዳለበት ያዛል።

## 5. ተከሳሽ አሰሪውን ድርጅት በሚለቅበት ሰዓት የሚኖረው ተጽእኖ

በ 90 ቀናት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ተከሳሹ ከድርጅትዎ በሚለቅበት ሰዓት፣ እና በድጋሚ የሚቀጠር ከሆነ፣ ይሄ የፍርድ ቤት ማዘዣ ሙሉ ለሙሉ ሳይጓደል ተግባራዊ ይደረጋል እና ተቆራጭ ገንዘቡን መቁረጡን ድርጅታችሁ ሊቀጥልበት ይገባል። ከ 91 ቀናት ወይም ከዚያ የበለጠ ቀናት ጊዜ ውስጥ ተከሳሹ ከድርጅትዎ በሚለቅበት ሰዓት፣ ይሄ ማዘዣ መቋረጥ አለበት እና ድርጅታቹህ የተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ የተቋረጠበትን ቀን በማስቀመጥ፣ የተመለሱትን መልሶች ቅጂ ለፍርድ ቤቱ መመለስ አለበት።

## 6. ተደራራቢ የተቋራጭ ማዘዣዎች ላይ የተለየ ቅድሚያ የመስጠት ሁኔታ

ለድርጅታቹህ በሰራተኛው ላይ የወጡ የፍርድ ቤት ተቆራጭ ማዘዣዎች ያላቹህ ከሆነ እና እስካሁን ተከፍለው ያላለቁ ከሆነ፣ ማዘዣው ላይ የተቀመጠውን ተቆራጭ ገንዘብ ከመቁረጣቹህ በፊት፣ እነዚህ የፍርድ ቤት ማዘዣዎች በወጡበት የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተቆራጭ ገንዘብ ጥያቄዎቹን ማስተናገድ ይኖርባቹሃል። በአንድ ተመሳሳይ ጊዜ ላይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የፍርድ ቤት ማዘዣ የደረሳቹህ ከሆነ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ማርሻል ቅድሚያ የተመታበት ሰዓት

ያለው ማዘዣ ቅድሚያ ይሰጠዋል።

## 7. ማስጠንቀቂያ እና የሕግ ስልጣኖች

የ 1971 የዲ.ሲ. ሸማቾች የክሬዲት መረጃ ጥበቃ አዋጅ ክፍል 6 (P.L. 92-200) በፍርድ ቤት የተወሰነ ውሳኔ ለማክበር ተቆራጭ ገንዘብ እንዲከፍል የታዘዘን ግለሰብ ያልከፈለው ገንዘብ ስላለ ወይም ገንዘብ ሊቆረጥበት ስለሆነ ብቻ አንድን ተቀጣሪ ሰራተኛ ከስራ ማሰናበት ይከለክላል። የፌደራል የደሞዝ ተቆራጭ አደራ ስምምነት ፈፃሚ [Federal Wage Garnishment] ሕግ በማንኛውም ባለዕዳነት የተነሳ የአንድ ተቀጣሪ ሰራተኛ ገቢ ተቆራጭ ሲደረግ እንደዚህ ዓይነት ከስራ ማሰናበቶችን ይከለክላል እና እንደዚህ ዓይነት የሕግ ጥሰት የሚፈጽሙ ቀጣሪ ድርጅቶች ወይም ባለቤቶቻቸው ከ $1,000 ዶላር የማይበልጥ የገንዘብ ወይም ከአንድ ዓመት የማይበልጥ የእስራት ቅጣት እንዲጣልባቸው ያስገድዳል።

**የዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የፍትሀ ብሔር ክፍል**

# ለተከሳሽ(በፍርድ ቤት ካሣ እንዲከፈል የተፈረደበት ወገን) ስለ ደሞዝ ተቆራጭ በተመለከተ ማስታወቂያ

## ለምንድን ነው ይሄንን ደብዳቤ የምቀበለው?

ይሄ የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የወጣ ተጨማሪ ማዘዣ ለአሰሪ ድርጅትዎ የተሰጠ የሕግ ሰነድ ቅጂ ነው። ይሄ ደብዳቤ ለእርስዎ እንዲሰጥ የተደረገው በዚህ ክስ መዝገብ ላይ የተጠቀሱት ከሳሽ በእርስዎ ላይ የገንዘብ ፍርድ ስለተፈረደላቸው ነው። የገንዘብ ፍርድ ለሌላ ሰው ("የፍርድ ቤት ካሣ የተፈረደለት ወገን") ሊከፍሉት የሚገባ የገንዘብ ዕዳ በተመለከተ የሚሰጥ የፍርድ ቤት ውሳኔ ነው። ከሳሽ (ወይም የብያኔ-የገንዘብ ባለቤት) ከእርስዎ ደሞዝ ላይ ተቆርጦ ገንዘባቸው እንዲከፈላቸው እየጠየቁ ነው። የገንዘብ ተቆራጭ ማለት ዕዳን ለመክፈል እያንዳንዱ የደሞዝ ክፍያ መክፈያ ክፍለ ጊዜ ላይ ከተቀጣሪ ሰራተኛው ደሞዝ ላይ ተቀናሽ የሚደረግ የገንዘብ መጠን ነው። የደሞዝ መቁረጡ ሂደት በዕዳ የታዘዘው ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ይቀጥላል።

## ደሞዜ ሊቆረጥብኝ ይችላል? አዎ ከሆነ፣ በምን ያህል መጠን?

የዲ.ሲ ሕግ አንዳንድ የደሞዝ መጠኖች እንዳይቆረጡ ያግዳል። ለምሳሌ፣ ከዲ.ሲ ዝቅተኛው የሚፈቀደው የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን በ 40 ሲባዛ በሳምንት መከፈል ከሚገባው ገንዘብ እኩል ከሆነ ወይም ካነሰ (በሌላ አገላለጽ፣ በዝቅተኛ የሚፈቀደው የሰዓት የደሞዝ ክፍያ መጠን መሰረት እኩል ሙሉ ሰዓት ወይም ከዚያ ባነሰ የሰሩ ከሆነ)፣ የሚያገኙት ገቢ ከተቆራጭ ነፃ ይሆናል እና ከደሞዝዎ ላይ ምንም ነገር አይቀነስም። ሆኖም ግን፣ ከዚያ በላይ ገንዘብ የሚያገኙ ከሆነ፣ አሰሪ ድርጅትዎ በፍርድ ቤት ዕዳ እንዲከፈለው ለተፈረደለት ግለሰብ (ከሳሽ) የደሞዝዎን የተወሰነ ክፍል በመቁረጥ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። የሚቆረጠው ገንዘብ ስሌት በፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የወጣ ተጨማሪ ማዘዣ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ነው።

## ማድረግ የምችለው ሌላ ነገር አለ?

ከተቆራጭ ገንዘብ የሕግ ከለላ ያሎት ከሆነ፣ ወይም በፍርድ ቤት ለተፈረደለት ከሳሽ ከደሞዝዎ በመቁረጥ ዕዳውን የመክፈል አቅም ያሎት ከሆነ፣ ምንም አይነት ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ አይጠበቅቦትም። ሆኖም ግን፣ በ ዲ.ሲ ሕገ ደንብ ቁጥር§ 16-572a መሰረት በገንዘብ አቅም ችግር የተነሳ የሚቆረጠው ገንዘብ መጠን እንዲስተካከልሎት ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ለማቅረብ፣ እርስዎ ወይም ጠበቃዎ አቤቱታ ማቅረብ አለብዎ። ከፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት ወይም ኦንላይን በድረገጽ www.dcourts.gov ላይ አቤቱታ የማቅረቢያ ቅጹን ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ፍርድ ቤቱ የወሰነው ውሳኔ እንዲቀለበስ ለማድረግ የሚችሉባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በገንዘብ አቅም ችግር የተነሳ ከደሞዝ ላይ የሚቆረጠውን የገንዘብ መጠን እንዲስተካከል አቤቱታ ያቀረቡ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ አዲስ ውሳኔ

እስከሚሰጥ ድረስ የደምዝ መቁረጥ ሂደቱ እንዲቆም ለቀጣሪ ድርጅትዎ የአቤቱታውን ቅጂ ወዲያውኑ ማቅረብ ይኖርቦታል።

የሕግ አገልግሎት ሰጪዎች ውስጥ የሚገኙ ጠበቃዎች በነፃ እገዛ ሊሰጥዎት ይችላሉ። የሕግ እገዛ ማግኘት ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ የሚከተለውን ይጎብኙ፡- www.dc.courts.gov/services/represent-yourself.

**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የፍትሀ ብሔር ክፍል**

______________________________፣ ከሳሽ

ከ. መዝገብ ቁጥር፦ ______________________

______________________________፣ ተከሳሽ

## <u>ለአሰሪ ድርጅት-ለአደራ ስምምነት ፈፃሚው መረጃ</u>

የሚከተሉት መረጃዎች የተከሳሹን ማንነት መለየት ላይ እንዲረዱ የቀረቡ ናቸው። እባክዎ ከዚህ ማረጋገጫ ጋር ለሚያያዙ ጥያቄዎች በፍርድ ቤት ለተወሰነለት ከሳሽ ጋር ይገናኙ።

| | |
|---|---|
| **ሙሉ ስም** | |
| **አድራሻ** | |
| **የ SSN የመጨረሻዎቹ 4 አሃዞች**<br>*ለፍርድ ቤቱ የሚገባ ከሆነ እንዳይታይ ይደረግ* | |

ይሄ የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የወጣ ተጨማሪ ማዘዣ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በዚህ ክስ መዝገብ ላይ የፍርድ ውሳኔው ላይ የቀረቡት የሚከተሉት መረጃዎች ትክክለኛ ናቸው። ልክ እንደ ወለድ እና ዕዳዎች የመሳሰሉ ሁኔታዎች መሰረት አጠቃላይ የገንዘብ መጠኑ ሊቀየር ይችላል። እባክዎ የተቀየረውን የገንዘብ መጠን ለመወሰን በፍርድ ቤት የተፈረደለትን ከሳሽ ያግኙ።

| | |
|---|---|
| **የፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ቀን** | |
| **ከወለድ በፊት እንዲከፈል የተወሰነው የገንዘብ መጠን** | |
| **ወለድ** | |
| **በአጠቃላይ የሚከፈለው ዕዳ መጠን** | |

| | |
|---|---|
| **በፍርድ ቤት የተፈረደለት ከሳሽ የሚገኙበት አድራሻ** | |
| **ስም** | |
| **ስልክ** | |
| **ኢሜይል** | |